## ፓኖራማ ቁጥር 97

መስከረም 26 ቀን 2003 ዓም

# የትዝብት አድማስ

## አገሩን ያስደፈረ

## በታሪክ ተመነጠረ !

የአባወራ ሚስት ራሷን አስከብራ ባሏን ካላስከበረች፥ባሏንም ራሷንም አዋርዳ ፥ ቤተሰቧን አሳፍራ፥ ልጆቿን በትና፥ ትዳሯንም አፍርሳ መና ሁና እንደምትቀር የታወቀ ነው:: በባሏም በኩል ተመሳሳይ ሂደትና መጨረሻ ነው የሚሆነው:: የአንድ ኅብረተሰብ መሠረቱና ምሶሶው ደግሞ የጠንካራ ትዳር መኖር ነው :: የኅብረተሰብን ሁኔታ ደግሞ ሳፋ ተደርጎ ሲታይና መሠረቱ በሀገር ደረጃ ከፍ ተደርጎ ሲመዘን ፥ የሀገርንና ሕዝብን ክብር ሊያስከብርም ሆነ ሊያዋርድ የሚችልው ፥ በወቅቱ የመንግሥት ሥልጣን የያዘው ሥርዓት ነው :: በዛሬ የኢትዮጵያ፥ ዜጎች ራሳቸው የሀገራቸው ባለቤቶች እያሉ ፥ ባዕዳንና ወያኔዎቹ ፥ የሀገሪቱን ኃብት እየተቀራመቷት ይገኛሉ :: በኃብት ዝርፊያውም አንዱ ከሌላው የበለጠ ለማግበስበስ እየተሻኮቱ ናቸው :: ዜጎቿም ፥ ለጉድ የጎለታቸው ብቻ ሳይሆኑ ፥ የበይ ተመልካችም ጭምር ሆነው ቀርተዋል :: ሀገራችን ኢትዮጵያ በረዥም ዘመን ታሪኳ ውስጥ በዕርግጥ የዚህ ዓይነት የታሪክ ምፀት አጋጥሟት አያውቅም :: <u>ባዕዳን እየበለፀጉ ፥ ዜጎቿ እየተቀራመዱ የሚኖሩበት ዘመን</u> !

የአገዛዙና የሥርዓቱ አራማጅ ቡድን ድርጊትና ባኅርይ፥ ለሀገርና ሕዝብ መከበርም ሆነ መዋረድ ተጠያቂ ነው::በአጭሩ፥ራሱን አስከብሮ ሌላውን ማስከበር የሰብዓዊና የመንግሥት ኃላፊነትና ግዴታ ተቀዳሚ ተግባር መሆኑ ነበረበት :: ግን ይህ በኢትዮጵያ አልሆነም :: ራሱን ያላከበረ ከሌላው ከበሬታን ሊጠብቅ አይችልም :: የኢትዮጵያ ሕዝብ በምንም ምክንያት ይሁን አጋጣሚ የሚያዋርደውንና ሀገሩንም ሰድቦ ለሰዳቢ የሚሰጥ መንግሥት ሊያገኝ አይገባውም ነበር ::ለታሪኩ ፥ለባኅሉ ፥ለዕምነቱ፥ለሰብዕናው፥ለመስተጋብሩ፥ለነፃነቱ ለወደፊቱም ተስፋውና ራዕዩ የሚገባውን መንግሥትና ሥርዓት ማግኘት አለበት :: ኢትዮጵያና ዜጎቿ ክብራቸውንና ታሪካቸውን ፥ ነፃነታቸውንና ሉዓላዊነታቸውን

አክብሮ የሚያስከብርላቸውን ሥርዓተ-መንግሥት የማግኘታቸው ጉዳይ አያጠያይቅም ። በምንም መሰፈርት ቢለካ ፥ በማነኛውም የፖለቲካ ትንታኔም ይሁን ፥ የርዕዮተ-ዓለም ዕይታ ቢገመገም ፥ በዘር ወይም ብሄረሰብ ልዩነት ላይ ላይ የተመሠረተ ሥርዓተ-መንግሥት ኢትዮጵያ ሀገራችን ላይ ሊመጠባት ባልተገባ ነበር ። አይ ፥ እንዲያው በደፈናው ፥ “ እያንዳንዱ ኅብረተ-ሰብ የሚገባውን መንግሥት ያገኛል ” ካልተባለ በስቀር ፥ ፥ በሃያ አንደኛው ምዕተ-ዓመት ውስጥ ያለቸው ሀገራችን፥ የወያኔ ዓይነት ዘረኛ ሥርዓት አራማጆች መቀለጃ ልትሆን አይገባትም ብንል ትክክል ነው ። ኢትዮጵያ፥ የባዕዳን መፈንጫና የኃብቷ መራኮቻ እንድትሆን በጭራሽ የሚገባት ሀገር መሆን አልነበረባትም ።

የወያኔ እህል ውሀ ፥ በውድ ባለመሆኑ በግድ መቆረጥ አለበት ። ይህ ደግሞ የሚሆነው በሕዝባዊ የነፃነት ትግል ብቻ ነው ። ይህም ራሱ ሲኬታማ የሚሆነው፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ የተባበረና የተዋሃደ ፥ ከፍተኛ መሥዋዕትንም በሚጠይቅ ቆራጥ ትግል ብቻ ነው ። ሌላ መፍትሄ የለውም ። ሌላውማ ሁሉ ተሞክሮ ተሞክሮ ፋይዳ እንዳላመጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተረድቶት ዛሬ ለሌላ የትግል አማራጭ እየተዘጋጀ ይገኛል። ለሕዝባዊ -ብሔራዊ ሁለንተናዊ አመፅ !

የሀገራችንን የፖለቲካ ፥ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሁኔታ በቅርብ የሚከታተሉ የውጭ ተመልካቾች እንደታዘቡት፥ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የተነሰራፋው ጠባብ ብሔረተኛ ሥርዓት ኅብረ-ብሄር ለሆነችውና ለታሪካዊቷ ኢትዮጵያ የሚስማማ እንዳልሆነ፥ ተመክሮአችንም በጥናትና ምርምር የተደገፉ ሰነዶችንም ያቀርባሉ ። የአንድ ሀገር የተፈጥሮ ሀብትም ይሁን ፥ ብሄራዊ ጥሪት ግልጋሎቱም ይሁን ጠቀሜታው ፥ ለመላው ዜጎቿ መሆን እንዳለበት የሚያከራክር ባይሆንም፥ዛሬ በሀገራችን ያለው በዘር ላይ የተማከለ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ሥርዓት፥ ሕዝብ ጎጅ ፥ ሀገር አጥፊ ፥ ተተኪውን ትውልድ አውዳሚ እንደ ሆነ ለሁሉም ዜጋ ግልፅ ሆኗል ። ለዚህም ነው የዚህ ሥርዓት አራማጆች እራሳቸውን እያዋረዱ ኢትዮጵያንና ዜጎቿንም እያዋረዱ ናቸው የሚባሉት። ራስን በሙስና መዘፈቅ ፥በወሲብ መዋረድ፥ሀገርንና ዜጋን መከፋፈል ፥ የሀገርን ለም የርሻ መሬት ለባዕዳን መቸብቸብ በህግና በታሪክ የሚያስጠይቅ መሆኑ የማይገባቸው ብቻ ሳይሆን ፥ ደንታ የሚኖራቸውም አይመስልም ። ታሪክ የሌለው ሥርዓት ፥ ለታሪክ ተጠያቂ መሆኑን እንደማያምንበት ሁሉ ፥ኅሌናም ሆነ ይሉኝታን የማያውቅ ሥርዓት አራማጅም እንደዚሁ የኅሌና ተጠያቂነት የሚባል ነገር፥ በእነርሱ መዝገበ-ቃላት ውስጥ ሊገኝ አይችልም። የሀገሪቱን ዜጎች ለስደት እየዳረጉ ፥የሕቡን ብሄራዊ ጥሪት ለግላቸውና ለባዕዳን መጠቀሚያ እያደረጉ ፥ የመላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ነፃነት እየገፈፉ ፥ ዘለዓለም ሕዝብን እየደለልን እንኖራለን ማለት፥የሕዝብን የማሰብ ችሎታ ዝቅ አድርጎ መገመት ብቻ ሳይሆን፥

*የታሪክንም ሂደት አለመገንዘብም ጭምር ነው ። በታሪክ ፥ በህግና በትውልድ ዘንድ ተጠያቂ ያደርገናል የሚል ሥርዓተ - መንግሥት አራማጆች በኢትዮጵያ እስካልመጡ ድረስ ፥ ሀገራችን ከአምባገነን አገዛዝ ትላቀቃለች ማለት ዘበት ነው ። ኢትዮጵያን ከማንኛውም ዓይነት አምባገነን ሥርዓት ነፃ አውጥቶ ፥ፍትኅ - ርትዕ የሰፈነበት ሥርዓተ - መንግሥት እውን የሚሆነው ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገራችን ሲመጣ ብቻ ነው ። እኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስንል እኮ፥ በእጅ የማይዳሰስ ፥ በዐይን የማይታይ ፥ በህዋው ላይ ብቻ የተንሳፈፈ ( አብስትራክት የሆነ ) የህልም እንጀራና ፥ በዕርጎ ባኅር መዋኘት ማለታችን አይደለም ። ይህንንማ ሃስቱም ተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች ሲያቀነቅኑት ነበር ።እርሱ አይደለም ! እኛ ዴሞክራሲ ስንል፥ገደብ በሌለው ነፃነት ሕዝቡ ሙሉ ተሳትፎ ያደረገበት ነፃ ምርጫ ተካሄዶ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለምንም ተፅዕኖ ወኪሉን በመምረጥ የሚያቋቁመው የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ማለታችን ነው ። ብዙሀኑን አሳታፊ ዲሞክራሲ በተግባር ሲተረጎም ማየት ፥ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዓይነተኛ የባኅርይና የተግባር መግለጫ እንደሆነ እናምናለን ። ዴሞክራሲ ህያው ሆነ የሚባለው እኮ አሳታፊ ዴሞክራሲ ሲሆን ነው ! በመሆኑም ሕዝብ ነፃነቱን ተጎናጽፎ ያለስጋት የሚያከናውነው ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ፥ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረትና የነፃነት ዋስትና መሆኑን ሁላችንም ማመን አለብን ። በረዥሙ የሰው ልጅ ታሪክ ሂደት ፥ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ፥ በዲሞክራሲ፥በሃይማኖት ፥ በሥልጣኔ ፥ በሶሻሊዝም ፥ በነፃ አውጭ ወዘተ .... ስም ብዙ ግፍ እንደተፈፀመባቸው ልዩ ልዩ መጽሐፍት ፥ ሰነዶችና ስንክሳሮች ፥ የመዘገቡት ሀቅ ነው ። የኢትዮጵያም ሕዝብ የዚህ ሂደት ስለባ እንደሆነ የቅርብ ትዝታውና የአሁንም ሁኔታ ያረጋግጥለታል ። የሚያሳዝነው ግን ፥ አሁንም እኛ ኢትዮጵያውያን የከፋው የመከራ ገመዳችን አለመቆረጡ ነው ። የመከራችንን ገመድ ለመቁረጥ ግን ፥ ገመዱ በስብሶ ይወድቅልናል ብለን ጊዜ ልንሰጠው አይገባም ። “ ሙት ይዞ ይሞታል ” እንደሚባለው ፥ እስከሚበሰብስ ጊዜ ከተሰጠው ፥ ወደማያባራ መከራ ሀገሪቱን አስገብቶ ለመጥፋት ጊዜ ያገኛል ። ይህ ከሆነ ደግሞ ፥ ወያኔ የመጨረሻ ዓላማው ተሳክቶለታል ማለት ነው !*

*መንበረ- መንግሥትን ከሚያህል ሥልጣን ላይ ተቀምጠው፥ በባኅርይም ሆነ በተግባር፥ ራሳቸውን እያዋረዱ፥ የሀገሪቱንም ክብርና ሞገስ በማዋረድ ፥ በኢትዮጵያ የረዥም ዘመን የመንግሥት ታሪክ፥ የወያኔ መሪዎች የመጀመሪያዎቹ ሆነዋል ።ይህንንም “ ክብረ- ወሰን ” መግኘት የሚፈልጉት በመሆኑ ፥እንኳን ደስ ያላችሁ የሚላቸው ሰው አላጡም ። በታሪካችን ደግሞ ፥ሀገራችን የውስጥም ሆነ የውጭ ጠላት አጥታ አታውቅም ። ታዲያ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ ፀሎቱም ሆነ ትግሉ ፥ ወያኔን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን ፥ ወያኔዎቹን አስወግዶ ፥ ኢትዮጵያን የሚያዋርድ ሌላ መንግሥትና ቡድን እንዳይመጣበትም ጭምር ነው ። ዛሬ*

የሚካሄደው ትግል የብሄራዊ ነፃነት ትግል የሆነውም ፥በዘረኝነት ላይ የተመሰረተን የአምባ-ገነን ቡድን አስወግዶ፥ በሌላ ቅርፅና መልክ የሚመጣን አምባገነን ቡድን ላለመቀበልም ጭምር ነው ።

በዚህ በተጀመረው አዲስ የኢትዮጵያ ዓመተ ምህረት፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዓመተ- ፍዳ ለማላቀቅ አዲስ የትግል ምዕራፍ መከፈት ወቅታዊና አንገብጋቢ ነው። ትግሉ በየትኛውም አቅጣጫ ሆነ፥ ርከን መፋፋም እንዳለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ወስኗል። የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ በደረቀ ወንዝ ተሻጋሪ ፥ በእባብ ሬሳ አስፈራሪ ፥የሞተ ፈረስ ጋላቢ ፥ የነጠፈ ወተት አላቢ፥ በወያኔ ጓሮ ተልከስካሽ፥ በፈረንጆች ፍርፋሪ ተቋዳሽ፥ በባዕድ ቋንቋ ረጋ-ሰራሽ በሆኑት የትግል አቀንቃኞች ሊታለል አይችልም ። ከእንግዲህ ወዲህ ! በአዲስ ራዕይ ፥ በአዲስ የትግል ዓላማና ስልት ላይ የተመሰረተ ትግል ማካሄድ፥ ለድል ዋስትና ይሆናል። ይህንን ሊያስገኙ የሚችሉት ደግሞ ፤<u>የኢትዮጵያን ማዕከላዊነት መነሻና መድረሻ በማድረግ የተሰለፉ ኃይሎች ብቻ ናቸው ።</u>የነፃነት ትግል ለማካሄድ፥ሁለት ልብ ይዞ መነሳት አይቻለም። ሁለት ባላ ተመርኩዞ ማንከስ ፋይዳ አያመጣም ። ሲበርድ በእጅ፥ ሲፋጅ በማንኪያ ፤ የሚባለው አባባል ምናልበት ለውጭ ዲፕሎማሲ ቋንቋ ይረዳ ይሆናል ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዘረኞች አምባገነን ጭቆና ለማላቀቅ እንታገላለን የሚሉ ክፍሎች ግን እርስ በእርሳቸው ሊነጋገሩ የሚችሉትና የሚገባቸውም ቋንቋ ፥ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅምና ስትራተጂያዊ ( ዘላቂ ዓላማ) ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ግድ ይላል ። <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ታሪክ የጋራ ራዕይና የወደፊት ተስፋ አለው ብለው የሚያምኑ ኃይሎች ተሰባስበው፥ ተባብረው- አብረው ከተነሱ የሀገራችንን የፖለቲካ መልከዐ-ምድር በመለወጥ ተዓምር እንደሚያመጡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥርጥር የለውም ። ይህ እንዳይሆን የሚከለክል አንዳችም ምድራዊ ኃይል እንደሌለም እናውቃለን</u> !!!!